# እየየና ወየታ፣ በቀጥቃጩ “መንግሥት” ለሚሰቃዩ ኢትዮጵያኖች



Source: www.satenaw.com

አንተ እግዢአብሔር ሆይ የፈጠርኸን!
ማየትስ ታየናለህ፣
ግን ጥሪያችን ትሰማ ይሆን?
ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ሆይ፤
የምትኖር በሰማይ።
እኛ በእምነት ዓይኖቻችን የምናይህ፤
አንተ ግን እኛን ማየት ብቻ ሳይሆን፣
ሐሳባችነንም ታነባለህ።
አንተ ፈጣሪያችን
ኢትዮጵያኖችም የሰጡህ ስም እግዚአብሔር፤
እስኪ ልጠይቅህ አንድ ነገር።
ዓለምን ስትፈጥር ኢትዮጵያን በወንዝ ከበብህ፤ - ዘፍጥረት 2:13
በነብዩ አሞጽም አማካይነት እንዲህ አልህ፤
“የእስራኤል ልጆች ሆይ፥
እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን?” - ትንቢተ አሞጽ 9፡7
እስኪ ልጠይቅህ አንድ ነገር፤
አንተ እግዚአብሔር።
አሁን ያለነው እኮ፣ የነሱ ዘር፣ ማንዘሮች ነን፤
ያለውን ግፍ ሁሉ፣ ራስ በራሳችን ስናመጣ፣ ምነው በጸጥታ ታዘብኸን።

**አንተ እግዚአብሔር፣ ማየትስ ታየናለህ፣**
**ማየት ብቻ ሳይሆን፣ ሐሳባችነንም ታነባለህ።**
**ግን ጥሪያችን ትሰማ ይሆን?**

ለአለፉት አርባ አራት አመታት፣
ተጽፏል፣ተመስክሯልም በኢትዮጵያ "ፍርድ ቤት።"
የኢትዮጵያ ልጆች በገዦቻቸው፣
"ታሰሩ፣ ተኮላሹ፣ ተደበደቡ፣ ተገደሉ፣
በገደል ሳይሞቱ፣ ዓይናቻቸው እያዩ ተወረወሩ፤
መቃብራቸውንም እንዲቆፍሩ ተገደው፣
ከነነብሳቸው፣ ሳይሞቱ፣ ተቀበሩ።"
እስኪ ልጠይቅህ አንድ ነገር፤
ኢትዮጵያኖች የሚሉህ አንተ እግዚአብሔር።
የተናገርኸው በኤርምያስ 29:11 - "ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ፤
ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ፣ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም።"
ምነው ያ ለኛ አይሰራም? (!)
እሪ እያልን ጮኸን፣ ምነው ጥሪያችን አትመልስም?
ልመናችነንም አትሰጠነም?
ምንጊዜም በኢትዮጵያ የሚደረገውን ታያለህ፣
በምኒልክ ግቢ ያሉ ሁሉ
እንደ አሚካላ ሾህ፣ እንደ መርዘኛ እባብና እንደ ሰይጣን ሆነውብናል!
ካድሬወቻቸውም በገንዘብ ተገዝተው
ደብዳቢወችና ገዳዮች ሁነዋል፣
የውጭ ሐገሩችም መሪታችነን ተቀራምተውብናል፤
ለትውልድ የሚተርፍ እዳም ተከማችቶብናል።

**አንተ እግዚአብሔር፣ ማየትስ ታየናለህ፣**
**ማየት ብቻ ሳይሆን፣ ሐሳባችነንም ታነባለህ።**
**ግን ጥሪያችን ትሰማ ይሆን?**

እባክህ በቃ በል፤ እኛም ያን አይተን፤
ኡ! ኡ! ያልነውን፣ ስለሰማኸን እንድናመሰግን።
ደግሚም እማጸንሃለሁ፤
እንደ እኔ፣ በለቅሶ የሚለምኑም እንዳሉ አውቃለሁ።
ስለዚህ፣ እባክህ፣ ጻሎታችን ስማን፣ ይቅርም በለን።
ካንተ የምጠባበቀው፤
በ 2010 ዓ. ም. እንደ እትዮጵያውያን አቆጣጠር
ነጻ እንድታወጣን ነው።

አንተ "እሹ፣ ታገኛላችሁ" ስላልህ
እንደ ሰይጣንና እንደ አሚካላ ያሉትን፣
ከመካከላችን ንቀልልን።

ይቅርታ ማድረግም እንድንችል፣ እርዳን፤!
መማለላችንና መማጸናችን እንደምትሰማ በማመን
አስቀድሜ እላለሁ፣ ተመስገን፣ አሜን።

© ለምለም ፀጋው፣ በሥር ቤት ላሉ ሁሉ ከምሥጋና ጋር፣ የሕሊና ነጻነትን ለተጎናጸፉ። ከታች በተጻፈው ድርጊት የተነሳሳ፤ March 26, 2018

http://www.satenaw.com/ethiopia-opposition-leader-arrested-again-teshome-borago-satenaw-columnist/